# ቤተሰቦች መብቶች አላቸው

ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ
የአካል ጉዳተኛነት ያለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ድርጊት(IDEA)
ክፍል ሐ ለቤተሰቦች የደህንነት ጥበቃ ሥነ ሥርዓት

ዲሲ የቅድመ ጣልቃ ገብነት ፕሮግራም (DC EIP)
የቅድመ ትምህርት ክፍል

# የስቴት ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (OSSE)
# ዲሲ የቅድመ ጣልቃ ገብነት ፕሮግራም (DC EIP)
# የቅድመ ትምህርት ክፍል

## የቤተሰብ መብቶች

- ቤተሰቦች ግምገማ የማግኘት መብት አላቸው
- ብቁ የሆኑ ቤተሰቦች ከመጀመሪያው ግንኙነት በኋላ በ 45 ቀናት ውስጥ የተቀናጀ ዕቅድ የማግኘት መብት አላቸው
- ብቁ የሆኑ ቤተሰቦች የአገልግሎት አስተባባሪውን የማግኘት መብት አላቸው
- ቤተሰቦች ግላዊነታቸው የማስጠበቅ መብት አላቸው
- ቤተሰቦች የመስማማት መብት አላቸው
- ቤተሰቦች መዝገቦቻቸውን የመገምገም መብት አላቸው
- ቤተሰቦች ስለ ልጆቻቸው እና ቤተሰባቸው በተመለከተ መዝገባቸው ላይ የሰፈረውን የመቀየር መብት አለ
- ቤተሰቦች የጽሁፍ ቅድመ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጣቸው መብት አላቸው
- ቤተሰቦች ሊረዱት የሚችሉት መረጃ የማግኘት መብት አላቸው
- ቤተሰቦች ያለመስማማት መብት አላቸው

# የስቴት ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (OSSE)

## ቤተሰቦች መብቶች አላቸው

የአካል ጉዳተኝነት ያለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ድርጊት(Individuals with Disabilities Education Act)፣ ክፍል ሐ፣ አገልግሎቶች እና ድጋፎች በተገቢ መልኩ፣ ፍትሃዊ፣ እና ምላሽ በሚሰጥ መልኩ እንደሚቀርቡ ለማረጋገጥ ለቤተሰቦች ደህንነት ጥበቃ ያቀርባል። የዚህ ቅድመ የደህንነት ሥነ ሥርዓት ሙሉ ጽሁፍ የፌደራል ደንቦች ኮድ (Code of Federal Regulations (CFR)) 34 ክፍል 303 ርዕስ ላይ ይገኛል። የእነዚህ የደህንነት ጥበቃዎች ማብራሪያ ለእርስዎ በሚመች መልኩ እዚህ ቀርቧል።

*ለጥያቄዎች ወይም ስለ መብቶችዎ የበለጠ ለማወቅ፣ በዚህ ያግኙን:*

- የአገልግሎት አስተባባሪዎ:
- ለልጅዎ የቀደምት ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች የሚያቀርበው ግለሰብ፥ ወይም
- DC EIP ሠራተኞች በ (202) 727-3665 ወይምosse.dceip@dc.gov።

## ቤተሰቦች ግምገማ የማግኘት መብት አላቸው

ለቅድመ ጣላቃ ገብነት ብቁ መሆን በአብዛኛው የሚወሰነው ልጅዎ (ከሦስት ዓመት በታች) የሆነው እሱ ወይም እሷ ዕድገት ላይ የሚያሳስብ ነገር በመገኘቱ ወደ DC EIP ሪፈራል ተልኮ ምርመራ ከተደረገበት በኋላ ነው። (34 C.F.R. § 303.321(a)(1)) ምርመራው የምርመራ መሳሪያን የሚቆጣጠሩ የዘርፈብዙ የሙያ ችሎታ ባላቸው ሁለት ውይም ከዚያ በላይ በሆኑ ላቀ ብቃት ባላቸው የስፔሻሊስቶች ቡድን መከናወን አለበት እና የልጅዎን ታሪክ፣ ዕድገት፣ የአሁኑን ጥንካሬውን እና ድክመቱን፣ እና የሕክምና፣ የትምህርት፣ እና ሌሎች መረጃዎችን መፈተሽ/መገምገም አለበት። (34 C.F.R. § 303.321(b)) ብቁ መሆንን የሚያሳይ አስቀድሞ ያለ የሕክምና ወይም ሌላ ሰነድ ካለ፣ በዚህ ጊዜ ምርመራው ላያስፈልግ ይችላል። (34 C.F.R. § 303.321(a)(3)(i)) ለቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ልጅዎ ብቁ እንደሆነ ከተረጋገጠ፣ እሱ ወይም እሷ ለቀደምት ጣልቃ ገብነት አገልግሎት ይመራል እና የግልሰብ የቤተሰብ የአገልግሎት ዕቅድ (IFSP) ይዘጋጅለታል። (34 C.F.R. § 303.342(a)) ልጅዎ ብቁ አለመሆኑ ከተረጋገጠ፣ በጽሑፍ እንዲያውቁት ይደረጋል እና የመቃወም እና ጉዳዩን በሽምግልና፣ ሰሚ ችሎት ወይም በግዛቱ የቅሬታ አቀራረብ ሂደት መሰረት የመፍታት መብት አሎት። (34 C.F.R. § 303.322)

## ብቁ የሆኑ ቤተሰቦች ከመጀመሪያው ግንኙነት በኋላ በ 45 ቀናት ውስጥ የተቀናጀ ዕቅድ የማግኘት መብት አላቸው

እያንዳንዱ ብቁ የሆነ ልጅ እና ቤተሰብ የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን ላይ – የግለሰብ ቤተሰብ አገልግሎት ዕቅድ (IFSP) – በጽሁፍ ዕቅዱን ለማዘጋጀት

ስብሰባ ላይ እንዲሳተፍ መደረግ አለበት። (34 C.F.R. § 303.310(a)) ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ፣ IFSP የሚያካትተው ስለ ቤተሰብዎ ግብአቶች፣ ቅድሚያ የሚሰጧቸው ነገሮች፣ እና ስለ ልጅዎ ያሎት ስጋቶች ላይ መረጃ፣ እንደዚህ ዓይነት መረጃ ለማካተት የሚስማሙ ከሆነ ነው። (34 C.F.R. § 303.344(b)) የ IFSP ግምገማ በእያንዳንዱ ስድስት ወራት ላይ መከናወን አለበት። (34 C.F.R. § 303.341(b)) ሆኖም ግን፣ ቤተሰቦች ከ IFSP ቡድን ጋር በማንኛውም ሰዓት ሂደቱን ለመገምገም እና IFSP ላይ ያሉ ሊከሰቱ የሚችሉ ለውጦች ላይ ለመወያየት የመጠየቅ መብት አላቸው። የዘመነ ግምገማ በየዓመቱ መሞላት አለበት።

ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ፣ በተጨማሪም IFSP የልጁን የአሁን የዕድገት ደረጃ፥ ለልጅዎ የታለመውን የሚለካውን ውጤቶች፥ ምን እና የት አገልግሎቶች እንደሚሰጡ፥ አገልግሎቶች መቼ እንደሚጀመሩ፥ እና አገልግሎቶች መቼ እንደሚከፈሉ ያካትታል። (34 C.F.R. § 303.344) በተጨማሪ፣ IFSP የልጅዎን ፍላጎት የሚያሟላ ወደ ቅድመ ትምህርት ወይም የቀደምት የልጅነት መርሀግብር ዕቅድ ያካትታል። (34 C.F.R. §§ 303.344(h) እና 303.209) የሽግግር ዕቅድ ማውጣት ውይይቶች በግምገማዎች እና ዓመታዊ IFSP ስብሰባዎች ላይ ይደረጋሉ። የሽግግር መስፈርቶች ልጅዎ ሦስት ዓመት ዕድሜ ሲሞላው ጊዜ መጠናቀቅ አለበት። (34 C.F.R. § 303.209(f))

IFSP ላይ የተዘረዘሩ አገልግሎቶች ወላጅ ስምምነቱን ከሰጠ በኋላ በተቻለ መጠን ወዲያውኑ ለልጁ መሰጠት አለባቸው፣ ይሄ በመደበኛው ወላጅ IFSP ን በፈረመ 30 ቀናት ውስጥ የሚከናወን ነው። (34 C.F.R. § 303.342(e))

## ብቁ የሆኑ ቤተሰቦች የአገልግሎት አስተባባሪውን የማግኘት መብት አላቸው

የልጅዎ IFSP የሚያካትተው ልጅዎን እና ቤተሰብዎን በ IFSP ውስጥ የተካተቱ የቀደምት ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን ማግኘት ላይ የሚያግዘው የአገልግሎት አስተባባሪ ስም ነው። (34 C.F.R. § 303.344(g)) ለምሳሌ፣ የአገልግሎት አስተባባሪዎ ልጅዎ የሚቀበለውን አገልግሎቶች ይከታተላል፣ የሚያስፈልግ ከሆነ፣ በ IFSP ውስጥ የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች ልጅዎ እንዲሚያገኝ ለማረጋገጥ ከአገልግሎት አቅራቢዎች እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል። እንደዚሁም የአገልግሎት አስተባባሪዎ ስለ መብቶችዎ እና በ DC EIP የሚቀርበውን የደህንነት ጥበቃ ሥነ ሥርዓት ላይ የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች ይመልሳል።

## ቤተሰቦች ግላዊነታቸው የማስጠበቅ መብት አላቸው

በአጠቃላይ ለመናገር፣ ስለ ልጅዎ ወይም ስለ ቤተሰብዎ የግል መለያ መረጃን የያዙ መዝገቦች በልጁ ወላጆች በጽሁፍ የተፃፈ ስምምነት ካልተሰጠ በስተቀር ለማንም ሰው መረጃው አይሰጥም። ሆኖም ግን፣ እንደዚህ ዓይነት መረጃዎች በግለሰብ የአካለ ጉዳተኝነት ድርጊት (IDEA) ወይም የቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና የግላዊነት ድርጊት (FERPA) መሰረት በሚጠቀሙበት ሰዓት ያለ ወላጅ ፈቃድ መጠቀም ይቻላል። የ IDEA ክፍል ሐ መስፈርቶችን ለማሟላት ዓላማ መረጃውን የሚሰበስቡ ፣ የሚጠብቁ እና የሚጠቀሙ ለተፈቀደላቸው ተወካዮች፣ የቢሮ ባለስልጣኖች ወይም የተሳታፊዎቹ ኤጀንሲዎች ሠራተኞች ያለ ወላጅ ፈቃድ እንዲያገኙ ይፈቀዳል። (34 C.F.R. § 303.414)

## ቤተሰቦች የመስማማት መብት አላቸው

የማጣሪያ ምርመራ፣ ምርመራ፣ ወይም ግምገማ ከመከናወኑ በፊት የእርስዎ ስምምነት ወይም ፈቃድ መሰጠት አለበት። እንደዚሁም የእርስዎ ስምምነት የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ከመጀመራቸው በፊት መሰጠት አለባቸው። (34 C.F.R. § 303.420(a)) ለተመረጠ አገልግሎት፣ ግምገማ ወይም ምርመራ ስምምነት ላለመስጠት ወይም የመረጡትን አገልግሎት፣ ምርመራ ወይም ግምገማ ሌሎች የቀደምት ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን፣

ሳያደናቅፉ ሐሳብዎን የመቀየር መብት አሎት። (34 C.F.R. § 303.420(d)) ስምምነትዎን እንዲሰጡ በሚጠየቁበት ሰዓት፣ ስለሚወጣው ሁሉም መዝገብዎ (ያለ ከሆነ) ላይ ስላለው መረጃ እና ለማን ይሄ መረጃ እንደሚሰጥ በጹሁፍ እንዲያውቁት መደረግ አለበት፣ እና ስለሚወጣው መረጃ የመቃወም አማራጭ አሎት። (34 C.F.R. § 303.7) የልጅዎ መዝገብ ወይም መረጃ ስለመውጣቱ ተቃውሞ ያሎት እንደሆነ በጽሁፍ መቅረብ አለበት።

### ቤተሰቦች መዝገቦቻቸውን የመገምገም መብት አላቸው

ከልጅዎ ጋር የሚገናኙ ማንኛውም የቅድመ ጣልቃ ገብነት መዝገቦችን መመርመር እና መገምገም ይችላሉ፣ እነዚህም የሚያካትቱት ግምገማዎች እና ምርመራዎች፥ የብቁነት ምዘናዎች፥ የ IFSP ዕድገት እና አፈፃፀም; ስለጅዎ የግልሰብ ተቃውሞዎች; እና ልጅዎን እና ቤተሰብዎን በተመለከተ በጠንካራ ጅማሬ ፕሮግራም የተሰበሰቡ፣ የተቀመጡ ወይም አገልግሎት ላይ የዋሉ ማንኛውም የቅድመ ጣልቃ ገብነት መዝገቦች ናቸው። (34 C.F.R. §303.401(b)(2)) እንደዚሁም ማንኛውም መዝገቦች ቅጂ መጠየቅ ይችላሉ። DC EIP እና የልጅዎ አገልግሎት አቅራቢ(ዎች) ያለምንም ማዘግየት፣ እና የልጅዎን IFSP በተመለከተ ያለ ማንኛውም ስብሰባ በፊት ወይም ስለ ክፍል ሐ በተመለከተ ስለልጅዎ የቀረበ ሰሚ ችሎት፣ እና ጥያቄው ከተነሳ ከአስር ቀናት በፊት ያላለፈ በማንኛውም ዓይነት ጉዳይ በፊት ጥያቄዎን መመለስ አለባቸው። (34 C.F.R. § 303.405) እንደዚሁም DC EIP ወላጅ ወይም የተፈቀደለት ወኪል፣ ወይም የ DC EIP ሠራተኛ ካልሆነ በስተቀር የልጅዎን ፋይል ያየውን ማንኛውም ግለሰብ መዝገብ ላይ ማስፈር አለበት። ይሄ መዝገብ የወገኑ ስም፣ መቼ ፈቃድ እንደተሰጠው፣ እና መዝገቦችን ለመጠቀም ግልሰቡ የተፈቀደለት ዓላማን ማካተት አለበት። (34 C.F.R. § 303.406) መዝገቦቹን የመመርመር እና የመገምገም መብትዎን ክፍያው በትክክል የማያግድዎት ካልሆነ፣ DC EIP ወይም የአገልግሎት አቅራቢ ቅጂ ሲጠየቅ ጊዜ ክፍያ እንዲያስከፍል ተፈቅዶለታል። DC EIP፣ ሆኖም ግን፣ የልጁን የቅድመ ጣልቃ ገብነት መዝገቦችን የመጀመሪያ ቅጂ ለወላጆች ያለምንም ወጪ ማቅረብ አለበት። 34 C.F.R. § 303.400(c)። በተጨማሪም፣ ከእያንዳንዱ የ IFSP ስብሰባ በኋላ ወላጆች ወዲያውኑ የእያንዳንዱን ምርመራ፣ ግምገማ እና IFSP ነፃ ቅጂ የማግኘት መብት አላቸው። (34 C.F.R. § 303.409) DC EIP የልጅዎ መዝገቦች ውስጥ ለመፈለግ ወይም መረጃ ለመፈተሽ ክፍያ እንዲያስከፍል አይፈቀድለትም። (34 C.F.R. § 303.409)

## ቤተሰቦች ስለ ልጆቻቸው እና ቤተሰባቸው በተመለከተ መዝገባቸው ላይ የሰፈረውን የመቀየር መብት አለ

በልጅዎ የቅድመ ጣልቃ ገብነት መዝገብ ላይ ያለው መረጃ ትክክለኛ ያልሆነ፣ የሚያሳስት፣ ግላዊነትን ወይም የልጅዎን ወይም የእርስዎን ሌሎች መብቶች ይጥሳል ብለው የሚያምኑ ከሆነ፣ DC EIP መረጃውን እንዲያርም መጠየቅ ይችላሉ። DC EIP ጥያቄው በተቀበለ ተቀባይነት ባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ መረጃውን ማስተካከል እንዳለበት እና እንደሌለበት ይወስናል። ከጥያቄዎ ጋር በተያየዘ DC EIP መረጃዎን የሚያስተካክል ከሆነ፣ DC EIP ጥያቄውን እንዳልተቀበለ እና ጥያቄ መጠየቅ እንደሚችሉ ያሎትን መብትዎን ማሳወቅ እና አለመግባባቱን ለመቅረፍ ሰሚ ችሎት እንዳዘጋጀ ማሳወቅ አለበት። (34 C.F.R. § 303.410)

## ቤተሰቦች የጽሁፍ ቅድመ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጣቸው መብት አላቸው

የልጅዎን መለየት፣ መመርመር፣ ወይም ምደባ ለመጀመር ወይም ለመቀየር ወይም ለእርስዎ ልጅ ወይም ቤተሰብ የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን አቅርቦት DC EIP ወይም አገልግሎት አቅራቢዎ ከማቅረቡ፣ ወይም ካለመቀበሉ በፊት ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ (ቢያንስ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ) በጽሁፍ የተፃፈ ማስጠንቀቂያ ሊደርስዎት ይገባል። ይሄ ማስጠንቀቂያ የታለመውን ውሳኔ/እርምጃ ዝርዝር መስጠት እና ለውሳኔው/እርምጃው ማንኛውም ምክንያት ማቅረብ አለበት። እንደዚሁም ሽምግልናን መጠየቅ እና የስቴት ቅሬታ ማቅረብ እና የፍትህ ሂደት ቅሬታን ጨምሮ፣ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ የእርስዎን መብቶች እና የቅሬታ ማቅረብ ሂደቶችን እንዲያውቁት ማድረግ አለበት። ይሄ ማስጠንቀቂያ በአብዛኛው ህዝብ በቀላሉ በሚረዳው መልኩ መፃፍ እና በእርስዎ ቀዳሚ ቋንቋ፣ ወይም እርስዎ በሚጠቀሙበት ሌሎች የመግባቢያ ዘዴዎች በኩል መቅረብ አለበት። (34 C.F.R. § 303.421)

## ቤተሰቦች ሊረዱት የሚችሉት መረጃ የማግኘት መብት አላቸው

DC EIP በዘር፣ በባህል፣ በሃይማኖት፣ ወይም በአካላ ስንኩልነት፣ ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ አድሎ አያደርግም። የቅድመ ጣልቃ ገብነት መረጃን ማስታወሻዎችን ጨምሮ በሚረዱበት መንገድ የማግኘት መብት አሎት። ማስታወሻዎች አብዛኛው ሕዝብ በሚረዳው መልኩ መፃፍ አለባቸው። ኢንግሊዘኛ ቀዳሚ ቋንቋዎ ካልሆነ፣ ፈጽሞ የማይቻል ካልሆነ በስተቀር፣ በቀዳሚ ቋንቋዎ መረጃን የማግኘት መብት አሎት። እንደ የምልክት ቋንቋ ወይም ብሬል የመሳሰሉ ሌላ ዓይነት የመግባቢያ ዘዴዎች የሚጠቀሙ ከሆነ፣ በዛ መልኩ መረጃ የማግኘት መብት አሎት። በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱት፣ ቅድሚያ የተፃፈው ማስታወሻ እንዲነበብልዎ እና እንዲብራራልዎ የመጠየቅ መብት አሎት። (34 C.F.R. § 303.421(2))

## ቤተሰቦች ያለመስማማት መብት አላቸው

የልጅዎን መለየት፣ መመርመር፣ ወይም ምደባ መቀየር ለማሰብ ወይም ሲቀይር ወይም ለእርስዎ ልጅ ወይም ቤተሰብ የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን አቅርቦት DC EIP ወይም አገልግሎት የተወሰደ ወይም አልቀበልም ያለው ነገር፣ ወይም የታሰበው እርምጃ በተመለከተ የቅድሚያ ጽሁፍ ማስታወሻ የማግኘት እና ያለመስማማት መብት አሎት። (34 C.F.R. § 303.421) የማይስማሙ ከሆነ፣ ሕጉ ከእነዚህ ዘዴዎች በአንዱ አለመግባባቱን በቶሎ ምላሽ ለመስጠት ይፈልጋል:

- ከስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of the State Superintendent of Education (OSSE)) መደበኛ የስቴት ቅሬታ ያቅርቡ፥
- ሽምግልና ይጠይቁ፥
- አድሎ የሌለው ሰሚ ችሎት የፍትህ ሂደት ይጠይቁ።

(34 C.F.R. § 303.430) እንደዚሁም፣ ያሎትን ቅሬታ እና ያልተስማሙበትን ለመወያየት ሁልጊዜ የእርስዎ አቅራቢ(ዎች) እና/ወይም DC EIP ሠራተኞችን እንዲያነጋግሩ ይበረታታሉ።
በተጨማሪም፣ DC EIP ወይም የአገልግሎት አቅራቢ(ዎች) ከላይ በተጠቀሱት ዘዴዎች ከእርስዎ ጋር ያሉትን አለመግባባቶች በቶሎ ለመፍታት ሊፈልግ ይችላል።

ሽምግልና በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የሁሉም ወገኖች አካል ነው እና የሚከናወነውም ሙያ ባላቸው በማያዳሉ ሽምጋዮች ነው። (34 C.F.R. § 303.431(b)) ከቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ጋር የተያያዙ ማንኛውም ጉዳይ በሽምግልና ሊፈታ ይችላል።

የሰሚ ችሎት ፍትህ ሂደት ስለ ቅድመ ጣልቃ ገብነት ዕውቀት ባላቸው የማያዳሉ ጉዳይ ሰሚ መኮንኖች የሚከናወን ነው። (34 C.F.R. § 303.443(c)) በሰሚ ችሎት የፍትህ ሂደት ወቅት የሚገኝ ወላጅ በጠበቃ እና/ወይም ስለ ቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ዕውቀት ባላቸው ሌሎች ግልሰቦች የማማከር አገልግሎት የማግኘት እና የመወከል፣

ማስረጃ የማቅረብ እና የመሟገት፣ መመርመር፣ የምስክሮችን እንዲጠሩ ማድረግ፣ ሰሚ ችሎቱ ከተከናወነ ቢያንስ ከአምስት ቀናት በፊት ለወላጅ ያልተሰጡ ማስረጃዎችን በሰሚ ችሎቱ ላይ እንዳይቀርቡ መከላከል፣ እና ያለምንም ወጪ የሰሚ ችሎት መኮንኑን ግኝቶች እና ውሳኔዎች የጽሁፍ ቅጂ የማግኘት መብት አላቸው። (34 C.F.R. § 303.444) እርስዎ፣ DC EIP፣ ወይም የእርስዎ አገልግሎት አቅራቢ(ዎች) ሰሚ ችሎት የፍትህ ሂደት የሚጠይቁ ከሆነ፣ ማንኛውም ነፃ ወይም ዝቅተኛ የሕግ አገልግሎት እና እዚህ አካባቢ የሚገኙ ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን እንዲያግዙት መረጃ የማግኘት መብት አሎት። (34 C.F.R. § 303.440(b)) እንደዚሁም ሰሚ ችሎት የፍትህ ሂደት ጠየቁም አልጠየቁም፣ በመጠየቅ ብቻ፣ ይሄንን መረጃ የማግኘት መብት አሎት። DC EIP ወይም የእርስዎ አገልግሎት አቅራቢ(ዎች) ለግዛቱ ፌደራል የብቁነት ዳኝነት ውሳኔውን ይግባኝ ካልጠየቁ በስተቀር፣ በሰሚ ችሎት ላይ የተሰጠው ማንኛውም ውሳኔ የመጨረሻ ነው። (34 C.F.R. §303.446(a))

የግዛቱ የቅሬታ ሂደት የሚተዳደረው በስቴት ኮምፕሌንት ኦፊስ OSSE ላይ ነው። መደበኛ የግዛት ቅሬታ በ DC EIP አይም ከልጅዎ አገልግሎት ሰጪዎች አንዱ ላይ፣ ክስ ያቀረቡ እንደሆነ OSSE የሚከተለውን ለማድረግ 60 ቀናት አለው፡

- የተሟላ የገለልተኛ ምርመራ ማጠናቀቅ፥
- በዚህ ቅሬታ የቀረበውን ክስ በተመለከተ፣ ቅሬታ አቅራቢው በቃል ሆነ በጽሁፍ ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርብ መፍቀድ፥
- DC EIP ወይም አገልግሎት አቅራቢው ቅሬታው ላይ ምላሽ እንዲሰጥ ዕድል ይሰጣል፥
- ሁሉንም ተዛማጅ መረጃዎች መገምገም እና DC EIP ወይም አገልግሎት አቅራቢው አካል በክፍል ሐ ላይ ያለውን የአካለ የአካለ ስንኩልነት ያለባቸው ግለሰቦች የትምህርት ድንጋጌን የጣሱ እንደሆነ በገለልተኛነት ማየት፥ እና
- በቅሬታ ውስጥ እያንዳንዱን ክስ ምላሽ ለመስጠት የጽሁፍ ውሳኔ መስጠት እና እንደዚሁም የሚከተለውን ያካትታል፥
  (i) ተጨባጭ ነገሮችን ማግኘት እና ድምዳሜ መስጠት፥ እና
  (ii) የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበትን ምክንያት ናቸው።

(34 C.F.R. § 303.433(a)) ምንም እንኳን አለመግባባት ከላይ በተጠቀሱት ማንኛውም ሦስት ዘዴዎች እየተፈታ ቢሆንም፣ እርስዎ ወይም የአገልግሎት አቅራቢዎ(ችዎ) ካልተስማማችሁ በስተቀር ልጅዎ የቅድመ ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶችን ማግኘቱን ይቀጥላል። (34 C.F.R. § 303.430(e))

<u>ለማግኘት፡</u>

<u>**Local Strong Start – ዲሲ የቅድመ ጣልቃ ገብነት ፕሮግራም(DC EIP):**</u>

**Andres Alvarado**
**የቅድመ ጣልቃ ገብነት ዳይሬክተር (Director for Early Intervention)**
Strong Start DC Early Intervention Program
Division of Early Learning
Office of the State Superintendent of Education 1371 Harvard Street NW, First Floor Washington, DC 20009
ስልክ: (202) 727-5853
ኢሜይል: Andres.Alvarado@dc.gov

**ለስቴት ክፍል**
**ሐ አለን ጄ ፊልፒስን (Allan J. Phillips) ያግኙ**
ስልክ: (202) 741-0475
ኢሜይል: Allan.Phillips@dc.gov

**ሽምግልና ለመጠየቅ ወይም ስለ ሽምግልና የበለጠ ለማወቅ፣ በዚህ ያግኙን:**

**የስቴት ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of the State Superintendent of Education (OSSE))**
1050 First Street, NE, Fourth Floor
Washington, DC 20002
ስልክ: (202) 698-3819
ኢሜይል: hearing.office@dc.gov
የድር ገጽ:
https://osse.dc.gov/service/special-education-mediation

**የሰሚ ችሎት የፍትህ ሂደት ለመጠየቅ ወይም ስለ ሰሚ ችሎት የፍትህ ሂደት በለጠ ለማወቅ፣ ያግኙን:**

**የስቴት ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of the State Superintendent of Education (OSSE))**
1050 First Street, NE, Fourth Floor
Washington, DC 20002
ስልክ: (202) 698-3819
ኢሜይል: hearing.office@dc.gov
የድር ገጽ:
https://osse.dc.gov/service/request-due-process-hearing

**መደበኛ የስቴት ቅሬታ ለማቅረብ ወይም ስለ ስቴትቅሬታ ማቅረብ የበለጠ ለማወቅ፣ በዚህ ያግኙን:**

**የስቴት ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of the State Superintendent of Education)**
**Division of Systems and Supports, K-12, State Complaint Office**
1050 First Street, NE, Fourth Floor
Washington, DC 20002
ስልክ: (202) 727-6436
ኢሜይል: osse.IDEAstatecomplaints@dc.gov
የድረ ገጽ:
https://osse.dc.gov/service/specialized-education-state- complaints

## የእኛ ተልዕኮ

የስትሮንግ ስታርት የቅድመ ጣልቃ ገብነት ፕሮግራም ተልዕኮ (Strong Start DC Early Intervention Program) የዕድገት መዘግየት እና አካል ስንኩልነት ያለባቸውን ከተወለዱ ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመታቸው ድረስያሉ ጨቅላ ሕጻናት እና እንቦቀቅላዎችን እንዲሁም ቤተሰቦችን ማግኘት እና ማገልገል ነው። ባህልን እና የቤተሰቦችን ፍላጎት የሚያሟላ የተዋሃደ አገልግሎት በእንክብካቤ መልኩ ለቤተሰቦች እናቀርባለን።

WE ARE WASHINGTON DC
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

የተሻሻለው ሜይ 2018 ነው።